## ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም የተካሄደውን አገራዊ ጠቅላላ ምርጫ አስመልክቶ
## ከየኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ሕብረት ለምርጫ (CECOE)
## የተሰጠ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት

***መግቢያ***

**ሰኔ 16 ቀን፣ 2013 ዓ.ም**

***መግብያ***

በስድስተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ የሲቪል ማህበራትን ተሳታፊነት ለማረጋገጥ እንዲያስችል 176 ማህበራት በጋራ በመሆን የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ሕብረት ለምርጫ የተሰኘ ድርጅትን መስርተዋል። ህብረቱ ገለልተኛ እና ከፓርቲ ፖለቲካ ነፃ የሆነ ድርጅት ሲሆን ምርጫው አካታችና ግልፅነት የተሞላበት መሆኑን ለማረጋገጥ የሚሰራ ድርጅት ነው። ይህ በሰኔ 14፣ 2013 በተካሄደው ምርጫ ላይ የሚሰጠው መግለጫ ህብረቱ በሰበሰበው መረጃ ላይ የተመሰረተ ቅድመ ግኝት ነው። የምርጫ ሂደቱ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ያልተጠናቀቀ ሲሆን ምርጫው በሰኔ 14 በተደረገባቸው ቦታዎች ላይ ስለነበረው የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ህብረቱ መረጃን ሰብስቧል። በቀጣይ ምርጫው ባልተካሄደባቸው ስፍራዎች የሚደረገውን ምርጫ ለመታዘብ ዝግጁ እንደሆነ ሊገልፅ ይወዳል። ከዚህ በተጨማሪ ህብረቱ በምርጫው ሂደት ውስጥ የተሳተፉ አካላትን እውቅና የሚሰጥ ሲሆን በተለይም በምርጫ ቀን ለረጅም ሰዓታት በሰልፍ ላይ በመቆየት ድምፃቸውን የሰጡ ዜጎችን፣ የምርጫ ቦርድን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና እጩዎቻቸውን፣ የፀጥታ ሀይሎችን እንዲሁም በምርጫው ሂደት ላይ የተሳተፉ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ሳያደንቅ አያልፍም።

ህብረቱ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ ባካሄደባቸው ሰባት ክልሎች እና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች፤ ከ3000 በላይ የሚሆኑ ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን አሰልጥኗል። ቋሚ ታዛቢዎች የታዘቧቸውን መረጃዎች በአዲስ አበባ ወደሚገኘው የሕብረቱ የመረጃ ማዕከል በጽሁፍ መልዕክት የላኩ ሲሆን፤ ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች ደግሞ በሚኖሩበት አካባቢ ያሉ ከምርጫ ጋር የተገናኙ ሂደቶችን እንዲሁም የድምፅ አሰጣጥ ሂደትን ከአንድ ምርጫ ጣቢያ ወደሌላ በመዘዋወር ታዝበዋል።

የምርጫ ቀንን ለመታዘብ በተዘጋጀው የትዝብት መጠይቅ ላይ በመመስረት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ፍቃድ የተሰጣቸው ታዛቢዎች የምርጫ ጣቢያዎችን ዝግጅት፣ አከፋፈት፣ የድምፅ አሰጣጥ እና ቆጠራ እንዲሁም የድምፅ ቆጠራ ውጤት በሚለጠፍበት ጊዜ የነበሩ ሁኔታዎችን ታዝበዋል። ሕብረቱ የምርጫ ቀን ትዝብቱን ስልታዊ በሆነ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ምርጫው በተከናወነባቸው በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ወጥነት እና ጥራት ያለው መረጃ ለማሰባሰብ የሚያስችል የትዝብት መጠይቆችን ተጠቅሟል። ይህ አሰራር የሕብረቱ ምልከታ፣ መረጃ አሰባሰብ እና ትንተና ሂደት ስልታዊ እንዲሆን ብሎም በመላ አገሪቱ በነበሩ የምርጫ ቀን ክንውኖች የያዙ መረጃዎች ለዜጎች እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ለማድረግ አስችሎታል። ከቋሚ ታዛቢዎች በተጨማሪ ከ150 በላይ ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን በማሰማራት በተንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች የተከሰቱ አሳሳቢ ኩነቶችን ለመረጃ ማዕከሉ እንዲልኩ ተደርጓል።

የህብረቱ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት ከምርጫ አሠራር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የምርጫ ምልከታ ግኝቶች ዋና ዋና ነጥቦች ያብራራል። ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት ህብረቱ ሰኞ፣ ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም በጎልደን ቱሊፕ ሆቴል በይፋ ከሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ፤ እንዲሁም ካሰራጨው የአሳሳቢ ኩነቶች መረጃ በተጨማሪ የቀረበ ነው። በዚህ መግለጫ ላይ የተካተቱት አንዳንድ መረጃዎች ሕብረቱ ከመረመራቸው ተጨማሪ የትዝብት ሪፖርቶች አንፃር መጠነኛ ልዩነት ሊያሳዩ እንደሚችሉ ሊገልፅ ይወዳል።

የዚህ መግለጫ ይዘት የምርጫ ጣቢያዎችን ዝግጅት፣ አከፋፈት፣ ድምጽ አሰጣጥ እና የቆጠራ ሂደትን ለመገምገም ምርጫ በተካሄደባቸው ሰባት ክልሎች እና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች ውስጥ ከተሰማሩ ታዛቢዎች እስከ ሰኔ 15 ቀን፣ 2013 ዓ.ም ሕብረቱ በተቀበላቸው ሪፖርቶች ላይ የተመሠረተ ነው።

## የታዛቢዎች ግኝት ማብራርያ

የሕብረቱ ታዛቢዎች ባቀረቧቸው ሪፖርቶች ላይ የተመሰረተው ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት በገለልተኝነት እና ያለአድሎ በተሰበሰበ መረጃ ላይ የተመሰረተ ነው። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግኝቶች ምርጫ በተካሄደባቸው ክልሎች እና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች ውስጥ የትዝብት ሪፖርቶቻቸውን በፅሁፍ መልእክት ካደረሱን ከ 2,200 በላይ ታዛቢዎቻችን በደረሰን መረጃ ላይ የተመሠረተ ነው። በተጨማሪ ህብረቱ አሳሳቢ ክስተቶችን ከቋሚና ተንቀሳቃሽ ታዛቦዎች የሰበሰበ ሲሆን ይህ መረጃ ከላይ የተሰበሰበውን መረጃ የሚያጠናክር ነው።

## በምርጫ ጣቢያዎች መገኘት

የምርጫ ጣቢያዎች ከጠዋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ ለድምፅ መስጠት ሂደት ዝግጁ  እንዲሆኑ የምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎች ከመከፈቻው ሰዓት ቀድመው በምርጫ ጣቢያዎች መገኘት እንዳለባቸው ይጠበቃል። የምርጫ ጣቢያዎችን አከፋፈት እና አዘገጃጀትን ለመገምገም ያስችል ዘንድ ሕብረቱ ታዛቢዎቹን ከጠዋቱ 11 ሰዓት ከ30 በፊት በምርጫ ጣቢያዎች እንዲገኙ አድርጓል። በዚህም መሠረት ትዝብት ከተደረገባቸው 93 በመቶ (2,052) በሚሆኑ ምርጫ ጣቢያዎች ላይ የምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎች የህብረቱ ታዛቢዎች በጣብያው ሲደርሱ በስፍራው መገኘታቸውን አረጋግጠዋል። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የሰጠውን የታዛቢነት ማረጋገጫ ባጆችን ያቀረቡ 97 በመቶ (2,128) በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) የሚሆኑ ታዛቢዎቻችን ወደ  ምርጫ ጣቢያ በመግባት እንዲታዘቡ ተፈቅዶላቸዋል።

## የምርጫ ጣቢያዎች አከፋፈት

በምርጫ ሂደት ውስጥ ከሚከናወኑት ቁልፍ ተግባራት አንዱ የድምፅ መስጫ ጣቢያ አከፋፈት ስርዓት ነው። ታዛቢዎች ከላኳቸው ሪፖርቶች 98 በመቶ (ማለትም 2,116 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች)  የሚሆኑት የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከጠዋቱ 1 ሰዓት በፊት መከፈታቸውን ያመለክታሉ። በምርጫ ህጉ ከተደነገገው በተቃራኒ 4 በመቶ (ማለትም 92 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) የሚሆኑት የህብረቱ ታዛቢዎች የታዘቧቸው ጣቢያዎች ህጉ በከለከላቸው ስፍራዎች ማለትም ፖሊስ ጣቢያዎች፣ ወታደራዊ ካምፖች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች በሚገኙባቸው ህንፃዎች ውስጥ መከፈታቸውን ታዛቢዎች ያቀረቡት ሪፖርት ያመለክታል።

በምርጫ ህጉ በተደነገገው መሰረት ከድምፅ መስጫ ቀን በፊት ባሉት አራት (4) ቀናት የምርጫ ቅስቀሳ ማካሄድ እንዲሁም ከድምፅ መስጫ ጣብያው በ200 ሜትር ርቀት የምርጫ ቅስቀሳ ቁሳቁስ መታየት በግልፅ ቢከለከልም ህብረቱ ካሰማራቸው ታዛቢዎች 12 በመቶ (ማለትም 256 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) የሚሆኑት ሰኔ 14፣ 2013 ዓ.ም በድምፅ መስጫ ጣብያዎች አቅራቢያ ቅስቀሳ መደረጉን ወይም የቅስቀሳ ቁሳቁስ መታየቱን ሪፖርት አድርገዋል።

## የምርጫ ጣቢያዎች አወቃቀር

በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የሚካሄደው የምርጫ ሂደት ከምርጫ ቦርድ ደንብ ጋር የሚስማማ መሆኑን ለማረጋገጥ የምርጫ ጣቢያ አዘገጃጀትን መገምገም ቁልፍ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም የሕብረቱ ታዛቢዎች በተዘጋጀላቸው መጠይቅ መሠረት የምርጫ ጣቢያዎችን አዘገጃጀት ገምግመው ሪፖርት አድርገዋል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች የምርጫ ጣቢያዎችን ተደራሽነት፣ የምርጫ ቁሳቁሶች አቅርቦትን እንዲሁም በሂደቱ ውስጥ የተሳተፉ ታዛቢዎች፣ የምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎች እና የፓርቲ ወኪሎችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ የተገኙት የመጀመሪያ ደረጃ ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው-

- ተደራሽነትን በተመለከተ በ95 በመቶ (ማለትም 2,039 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) ያህል ታዛቢዎች የተገኙባቸው የምርጫ ጣብያዎች ለወንዶችም ሆነ ለሴት መራጮች በእኩል መጠን በቀላሉ በሚገኙበት ስፍራ የተቋቋሙ ነበሩ።  በተያያዘ መልኩ ታዛቢዎች ከታዘቧቸው የምርጫ ጣብያዎች 13 በመቶ (ማለትም 285 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) የሚሆኑት ለአካል ጉዳተኞች እና ለመንቀሳቀስ ለሚቸገሩ መራጮች (ማለትም በእድሜ የገፉ ዜጎች፣ ህፃናት ያዘሉ እናቶች ወዘተ) ያለረዳት ተደራሽ አለመሆናቸውን ታዛቢዎች ገልፀዋል።

- ከታዛቢዎች በተገኘው መረጃ መሠረት 99.8 በመቶ (ማለትም 2,133 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ መስጫ ሣጥኖች ከመታሸጋቸው በፊት ባዶ መሆናቸው በግልፅ እንዲታይ ተደርጓል።
- የምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎችን በሚመለከት ታዛቢዎች ባቀረቡት ሪፖርት መሠረት በአማካይ አራት የምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎች ህብረቱ በታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎቹ ተገኝተዋል። ታዛቢዎቻችን በተገኙባቸው ጣቢያዎች በአማካይ ሁለት ሴት የምርጫ አስፈፃሚዎች የነበሩ ሲሆን ከእነዚህ መካከል 20 በመቶ (ማለትም 420 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) በሚሆኑት ጣቢያዎች ውስጥ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊዎች ሴቶች ነበሩ።
- በ91 በመቶ (ማለትም 1,937 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) ትዝብት በተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ሌሎች ታዛቢዎች በመከፈቻው ሰአት በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ታዛቢዎች የተገኙ ሲሆን በተመሳሳይ በ89 በመቶ (1910) የምርጫ ጣቢያዎች በተከፍቱበት ወቅት የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች ተገኝተው ነበር።

## ድምጽ አሰጣጥ

ከምርጫ ጣቢያዎችን አወቃቀር እና አከፋፈት ቀጥሎ ቀጣዩ ወሳኝ ጉዳይ በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ ውስጥ የሚኖረው የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ነው። የህብረቱ ታዛቢዎች የምርጫ ሂደቱን መታዘብን በተመለከተ፣ የድምፅ አሰጣጥ መመርያዎች መከበርን፣ በድምፅ አሰጣጡ ወቅት የኮቪድ19 መመርያዎች መከተልን እንዲሁም በጣቢያው ወይም በጣቢያው አካባቢ የፀጥታ ስጋቶችን መገምገምን በተመለከተ የተለያዩ ጥያቄዎችን መልሰዋል። ህብረቱ በድምጽ አሰጣጥ ሂደት በደረሱት ሪፖርቶች ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ግኝቶች አስቀምጠዋል።

- በምርጫ ቦርድ መመርያ መሰረት ታዛቢዎች በኮቪድ19 ምክንያት እስካልሆነ ድረስ በምርጫ ጣብያው በመገኘት ሙሉ የምርጫ ሂደቱን የመታዘብ መብት እንዳላቸው ተደንግጓል። በዚህ መሰረት 94 በመቶ (ማለትም 1,975 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) የሚሆኑት የህብረቱ ታዛቢዎች የምርጫ ሂደቱን ያለገደብ መታዘብ መቻላቸውን የተሰበሰበው መረጃ ያሳያል። ነገር ግን ከኮቪድ -19 መመሪያ ጋር ባልተያያዙ ምክንያቶች 1 በመቶ (ማለትም 12 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) የሚሆኑት የህብረቱ ታዛቢዎች በድምፅ አሰጣጥ ወቅት የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ እንዲቆዩ አልተፈቀደላቸውም። ከዚህ በተጨማሪ 6 በመቶ (ማለትም 119 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) የሚሆኑ የሕብረቱ ታዛቢዎች በኮቪድ19 መመሪያ ምክንያት የምርጫ ጣቢያውን ለቀው እንዲወጡ መጠየቃቸውን ተናግረዋል። ህብረቱ ሁሉም ዕውቅና የተሰጣቸው ታዛቢዎች በምርጫው ሂደት እንዲካፈሉ የሚጠብቅ ቢሆንም፣ በምርጫ ጣቢያዎች አወቃቀር ምክንያት እንዲሁም በኮቪድ19 ከግምት ውስጥ በማስገባት ከድምጽ መስጫ ጣቢያው እንዲለቁ ሊጠየቁ እንደሚችሉ ይታወቃል።
- ህብረቱ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢይዎች 96 በመቶ (ማለትም 2,020 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) የሚሆኑት በድምፅ አሰጣጥ ወቅት እንዲገኙ የተፈቀደላቸው አካላት ብቻ ተገኝተዋል ብለው ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን በአንፃሩ በ86 ክስተቶች በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ እንዲገኙ ያልተፈቀደላቸው ሰዎች መኖራቸውን ታዛቢዎች ገልጸዋል፡፡
- ከሕብረቱ ታዛቢዎች የደረሱን ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት 89 በመቶ (ማለትም 1,879 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) የሚሆኑ የምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎች ለመራጮች የድምፅ መስጫ ወረቀት ከመስጠታቸው በፊት ህጋዊ ማህተም እንዳደረጉ ተገልጿል። ሆኖም በ11 በመቶ (ማለትም 226 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) ያህሉ ጣብያዎች ይህ የሂደቱ ወሳኝ ተግባር ሙሉ በሙሉ እንዳልተጠበቀ መረጃዎች ያሳያሉ።
- ሌላው ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ የሕብረቱ ታዛቢዎች በተገኙባቸው የምርጫ ጣቢያዎች 17 ከመቶ (ማለትም 366 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) መራጮች ድምጽ ከመስጠታቸው በፊት የማይለቅ የጣት ቀለም አልተደረገላቸውም። ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች 10 በመቶው (ማለትም 198 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) የደምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ምስጢራዊነት ሙሉ በሙሉ አልተከበረም፡፡ በአንፃሩ 98 በመቶ (ማለትም 2,073 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) ታዛቢዎቻችን በተገኙባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ መስጫ ሳጥኖች የድምፅ መስጠት ሂደቱ እስኪጠናቀቅ በሚታይ ቦታ እንዲቀመጡ ተደርጓል።

- በ39 በመቶ (ማለትም 829 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች መራጮች በምርጫ መዝገብ ዝርዝሩ ላይ ባለመገኘታቸው ምክንያት እንዲመለሱ የተደረገ ሲሆን 6 በመቶ (ማለትም 114 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች)በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች መራጮች በምርጫ መዝገብ ዝርዝሩ ውስጥ ቢኖሩም ሳይመርጡ ተመልሰዋል።
- ኮቪድ 19 ሌላኛው ሕብረቱ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የምርጫ ትዝብት ያደረገበት አንዱ ነጥብ ነው። በዚህም መሠረት የመራጮችንም ሆነ የምርጫ አስፈፃሚዎችን የኮቪድ 19 መመሪያዎች አከባበር የሚመዝኑ ጥያቄዎችን በምርጫ ትዝብት መጠይቁ ውስጥ አካቷል። የህብረቱ የመጀመሪያ ደረጃ የትዝብት ሪፖርት እንደሚያሳየው 28 በመቶ(ማለትም 601 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) የምርጫ አስፈፃሚዎች በድምፅ መስጠት ሂደቱ ውስጥ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭንብሎችን በተሟላ ሁኔታ እንዳልተጠቀሙ ታይቷል። ይህ ቁጥር ከመራጮች ጋር በተያያዘ ወደ 62 በመቶ (ማለትም 1,312 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) ከፍ ብሎ ታይቷል። የሕብረቱ ታዛቢዎች ከታዘቧቸው የምርጫ ጣቢያዎች በ4 በመቶ (ማለትም 84 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች)ያሁሉ ከቦርዱ አሰራር በተፃረረ መልኩ መራጮች መደበኛ የአፍና እና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል ባለማድረጋቸው ምክንያት እንዲመለሱ ተደርገዋል።

## የድምፅ ቆጠራ

የድምፅ ቆጠራ በምርጫ ወቅት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው የምርጫ ሂደት አካል ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በድምፅ መስጫ እለት ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ መዘጋት ከነበረበት ወቅት (ማለትም ከምሽቱ 12 ሰዓት) እንዲራዘም በመወሰን የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ባልተጠናቀቀባቸው ጣቢያዎች እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት እንዲቀጥል አድርጓል። ይህ መራጮች ድምፃቸውን መስጠት እንዲችሉ እድል የሚፈጥር ቢሆንም የቆጠራውን ሂደት ከማዘግየቱ በላይ እንዲሁም ህብረቱ በቆጠራው ዙርያ በሰበሰበው መረጃ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። በተጨማሪም በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ እንዲሁም ቆጠራው ወደ ቀጣዩ ቀን እንተላለፍ ወይም በአንዳንድ ቦታዎች እንዲሰረዝ መወሰኑ የሚታወቅ ነው። ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ የማጣራት ስራዎችን ህብረቱ እየሰራ ሲሆን ይህ የመጀመርያ ደረጃ ሪፖርት የመጨረሻው አለመሆኑን ታሳቢ በማድረግ የሚከተሉትን ግኝቶች አስቀምጧል።

- የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መመርያ ባከበረ መልኩ በ95 በመቶ (ማለትም 1,983 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) ያህሉ ታዛቢዎች በተገኙባቸው ጣቢያዎች የድምፅ ቆጠራ ሂደቱን እንዲታዘቡ ተፈቅዶላቸው ነበር።
- ህብረቱ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች በ99 በመቶ(ማለትም 2,043 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) ያህሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የድምፅ መስጫ ወረቀቶች በጣቢያው የተቆጠሩ ሲሆን በ93 በመቶ (ማለትም 1,927 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች)ያህሉ የክልል እና የከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች የድምፅ መስጫ ወረቀቶች በጣቢያው ቆጠራዎች መካሄዳቸውን ታዝበዋል።
- በታዛቢዎች ሪፖርት መሰረት በ1 በመቶ (ማለትም 20 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) በድምፅ ቆጣራው ወቅት ጣልቃ ገብነት እንደነበረው ተገልጿል።
- በተጨማሪም በቆጠራው ሂደት ወቅት በአማካይ 4 የፓርቲ ወኪሎች እንደተገኙ ከታዛቢዎች የተሰበሰቡ ሪፖርቶች ያሳያሉ። በተጨማሪም የህብረቱ ግኝቶች እንደሚያሳዩት በ14 በመቶ (ማለትም 297 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች)ያህሉ ህብረቱ በታዘባቸው ጣቢያዎች የፓርቲ ወኪሎች በማመሳከርያ ቅፁ ላይ እንዳልፈረሙ መረጃዎች ያሳያሉ።
- የቆጠራ ሂደቱ ሲጠናቀቅ በምርጫ ቦርድ መመርያ ላይ ከተቀመጡ ወሳኝ ተግባራት መካከል የማመሳከርያ ቅፁን ከጣብያው ውጪ በሚታይ ቦታ በአንድ ሰዓት ውስጥ መለጠፍ አንዱ ነው። ሆኖም 27 በመቶ (ማለትም 568 በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች) በሚሆኑት ህብረቱ በታዘባቸው ጣቢያዎች ማመሳከርያ ቅፁ በዚህ መልኩ እንዳልተለጠፈ መረጃዎች ያሳያሉ።ይህ በእንዲህ እንዳለ አንዳንድ ታዛቢዎች እንገለፁት በምርጫው ቀን ማግስት የማመሳከርያ ቅፁ በስፍራው ተለጥፎ ነበር።

## አሳሳቢ ኹነቶች

በምርጫ ሂደት እና በቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ መረጃዎችን ከመሰብሰብ በተጨማሪ ታዛቢዎች በምርጫ ቀን በርካታ አሳሳቢ ኩነቶችን ሪፖርት አድርገዋል፡፡ የሕብረቱ የአሳሳቢ ኹነት ሪፖርቶች አጠቃላይ የምርጫ ሂደቱ ተዓማኒነት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን ይመለከታሉ። የአሳሳቢ ኹነቶች የምርጫ ጣቢያዎችን አለመከፈት፣ የድምፅ መስጠት እና የቆጠራ ሂደት መቋረጥ፣ የታጣቂ ኃይሎች መገኘት፤ እንዲሁም ከህግ አግባብ ውጪ የሆኑ የድምፅ አሰጣጥ እና ቆጠራ ሂደቶችን ያካትታሉ። በድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ የህብረቱ ታዛቢዎች እስከዛሬው ዕለት ድረስ ከ400 በላይ አሳሳቢ ኹነቶችን ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 338 ያህሉን የሕብረቱ የመረጃ ማዕከል አጣርቶ በማረጋገጥ በዚህ መግለጫ ላይ አካቷል። ሕብረቱ አሁንም የአሳሳቢ ኩነት ሪፖርቶችን ከታዛቢዎቹ እየተቀበለ እና እያጣራ ሲሆን፤ አዳዲስ ግኝቶቹን በመጨረሻው የምርጫ ትዝብት ሪፖርቱ ላይ አካቶ ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚያደርስ ይሆናል።

በዚህ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት በድምፅ መስጫው ዕለት ከታዩት አሳሳቢ ኩነቶች መካከል አብዛኛዎቹ፤ የምርጫ ቁሳቁሶች መጓደል፣ ታዛቢዎች እንዲታዘቡ ያለመፍቀድ፣ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ እንዲገኙ ያልተፈቀደላቸው ሰዎች መገኘት እና በድምጽ አሰጣጥ እና በመቁጠር ወቅት ማስፈራራት እና ትንኮሳዎችን ማንሳት ይቻላል፡፡

- በአጠቃላይ የምርጫ ቁሳቁሶች እጥረት ወይም ጉድለቶች መኖራቸውን የሚያስረዱ 138 ሪፖርቶች ለሕብረቱ ደርሰዋል። ለምሳሌ በተለይም በአዲስ አበባ ፣ በቤንሻንጉል ጉምዝ ፣ በጋምቤላ እና በሲዳማ ያሉ ታዛቢዎች የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ፣ የመራጮች መዝገብ እና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች እጥረት ማጋጠሙን ሪፖርት አድርገዋል፡፡
- በድምሩ 40 ያህል የህብረቱ ታዛቢዎች መታዘብ እንዳይችሉ መከልከላቸውን ሪፖርት አድርገዋል። በኦሮምያ ክልል አንዳንድ ታዛቢዎቻችን እንደገለፁልን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ አስተባባሪዎች ከቦርዱ ዕውቅና የተሰጣቸው ታዛቢዎች ዝርዝር ሊደርሰን ይገባል በሚል እምነት የመታዘቢያ ባጅ የያዙ የሕብረቱ ታዛቢዎች እንዳይታዘቡ ክልከላ አድርገዋል።
- የሕብረቱ ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎቹ ውስጥ እንዲገኙ ያልተፈቀደላቸው ሰዎች መገኘታቸውን የሚያስረዱ 30 ሪፖርቶች አድርገዋል። ለአብነት በአማራ ክልል የተሰማሩ የሕብረቱ ታዛቢዎች በተለይም በአንዳንድ አካባቢዎች ሊቀመንበሩን ጨምሮ የቀበሌ ሰራተኞች በድምጽ መስጫ ወቅት በጣቢያዎች ውስጥ ተገኝተዋል።
- የሕብረቱ ታዛቢዎች በ17 የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ማዋከብን እና ማስፈራራት መመልከታቸውን ሪፖርት አድርገዋል። በተወሰኑ የጋምቤላ እና የአማራ ክልሎች አካባቢዎች የፖለቲካ ፓርቲ አባላት በድምጽ መስጠት ወቅት መራጮችን እና የምርጫ አስፈፃሚዎችን ሲያስጭንቁ እና ሲያስፈራሩ እንደነበር ታዛቢዎቻችን ሪፖርት አድርገዋል።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የአሳሳቢ ኩነት ሪፖርቶች በምርጫ ሂደቱ ላይ የታዩ ተግዳሮቶችን የሚያሳዩ ናቸው።

## ማጠቃለያ

የኢትዮጲያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ሕብረት ለምርጫ /CECOE/ 6ኛው አገራዊ ምርጫን በመታዘብ ሂደት ያጋጠሙት ውስንነቶች እንደተጠበቁ ሆነው በምርጫው ሂደት ውስጥ ከዚህ በታች የተመለከቱትን በጎ ጎኖች እና ሊሻሻሉ የሚገቡ ነጥቦችን መታዘብ ችሏል፡፡

**በምርጫው ሂደት በበጎ ጎኖች የተመለከትናቸው**

ምርጫው ሠላማዊ ሆኖ ማለፉ፤

1. በድምፅ መስጠት ሂደቱ አንዳንድ ጉድለቶች እና ክፍተቶች የታዩ ቢሆንም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ክፍተቶቹን ለመሙላት ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት ጥረት ማድረጉ፤
2. መራጩ ሕዝብ በነቂስ በመውጣት በምርጫው ከመሳተፉም በተጨማሪ ድምፁን ለመስጠት በትእግስት መጠበቁ፤
3. ተፎካካሪ ፓርቲዎች የምርጫው ሂደት በሰላም እንዲጠናቀቅ ያደረጉት አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑ፤
4. ሕብረቱ በታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የተመለከተው የሴቶች ንቁ ተሳትፎ፤

5. የምርጫ ጣቢያዎቹ ለአካል ጉዳተኞች፤ ሕጻናት ለያዙ እናቶች፣ ለአቅመ ደካማ አዛውንቶች እና ሌሎች ድጋፍ ለሚሹ ዜጐች በተቻለ መጠን አመቺ እንዲሆን ጥረት መደረጉ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

**በምርጫው ሂደት የተመለከትናቸው ውሱንነቶች**

1. ጥቂት የምርጫ ጣቢያዎች ዘግይቶ መከፈት፤ የምርጫ ቁሳቁሶች መጓደል በመራጮች ላይ ያስከተለው አላስፈላጊ መጉላላት፤
2. የምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት በተመለከተ በአንድ የምርጫ ጣቢያ 1500 መራጮች መስተናገዳቸው በተጨባጭ ለአንድ መራጭ ድምፁን ለመስጠት ከሚወስደው ጊዜ አንፃር በቂ ሆኖ አለመገኘቱ ለብዙዎች መራጮች መጉላላትና ለምርጫ ጊዜ መራዘም ምክንያት መሆኑ፤
3. በምርጫው እለት በጥቂት የምርጫ ጣቢያዎች እንዲገኙ ያልተፈቀደላቸው ሰዎች መገኘታቸው እና የምርጫ ቅስቀሳ ሁኔታዎች መታየታቸው፤
4. ምርጫውን ለመታዘብ እንዲቻል ለታዛቢዎች የሚሰጠው ፈቃድ (ባጅ) አሰጣጥ ሂደት የተጓተተ ከመሆኑም በላይ የተደጋገሙ ባጆች መታተማቸው፤

ከላይ የተመለከቱትን የምርጫ አፈፃፀም በጎ ጎኖችንና ውሱንነቶችን በማገናዘብ ሕብረቱ የሚከተለውን አስተያት ያቀርባል፡፡

1. ምርጫ ቦርድ ከላይ የተጠቀሱት ውሱንነቶች ለወደፊት እንዳይከሰቱ አስፈላጊ የሆኑ የህግ፤ የአስተዳደር፤ የአደረጃጀት፤እና የአቅርቦት ማሻሻያዎች እንዲያደርግ ለማስገንዘብ እንወዳለን፡፡
2. ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫው እለት ምርጫው በሰላም እንዲጠናቀቅ ያሳዩትን ጥረት እንዲቀጥሉ ሕብረቱ ጥሪውን ያቀርባል፡፡
3. ለታዛቢ የሲቪል ማህበራት እና ለታዛቢዎች የሚሰጠው የታዛቢነት ፈቃድ ሂደት ባጠረ እና ታዛቢን በሚያበረታታ መልኩ እንዲታረም ይጠይቃል፡፡

በመጨረሻም ሕብረቱ በምርጫው መታዘብ ሂደት የተሳተፉትን አባል ድርጅቶች እና በሺዎች የሚቆጠሩ ፈቃደኛ ታዛቢዎች ጊያቸውን፤ ለገንዘባቸውንና ለጉልበታቸው ሳይሳሱ ምርጫው ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን ላደረጉት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ምስጋና ማቅረብ ይወዳል፡፡